MINNESOTA DEPARTMENT OF HEALTH

# የኮቭድ-19 ክትባቶች፡- በአስራዎቹ እድሜዎች ያሉ ማወቅ ያለባቸው ነገሮች

## ጽሁፍ

በአካል ወደ ትምህርት ቤት ለመመለስ ጓጉተዋል? ተለይተዉ በመቀመጥዎ ምክንያት ስፖርቶች ወይም ሌሎች ተግባራት እንዳይቋረጡ ይፈልጋሉ? ከቤተሰብ ወይ ጓደኞች ጋር መዝናናት መቻል ይፈልጋሉ? የኮቭድ-19 ክትባቶች ወደእነዚህ ሁሉ ነገሮች መመለሻ መንገድ ናቸው።

ለወጣቶች እና ወላጆቻቸው ከመከተባቸው በፊት ጥያቄዎች መጠየቃቸው የተለመደ ነው። ጥያቄ ካልዎት፣ ዶክተር ይጠይቁ። የተወሰኑ ፈጣን መረጃዎችን እነሆ፡-

- የኮቭድ-19 ክትባቶች ደህንነታቸው የተጠበቁ ናቸው።
- ለአዋቂዎች ጥናት እንደተደረገባቸዉ ሁሉ፣ እድሜያቸው በአስራዎቹ ቤት ላሉትም ጥናት ተደርጎባቸዋል፣ ስለዚህ እንደሚሰሩ እና ደህንነታቸው እንደተጠበቀ እናውቃለን።
- የኮቭድ-19 ክትባት ነጻ ነው እንዲሁም ID ወዪም መታወቅያ ማሳየት የለብዎትም።
- የኮቭድ-19 ክትባቶች መካንነትን አያስከትሉም።

ማንም ሰዉ መርፌ መወጋትን አይወድም፣ ነገር ግን ዘና እንዲሉ የሚረዱዎት ነገሮች አሉ።

- በጆሮ ማዳመጫ የሚወዱትን ሙዚቃ ያዳምጡ።
- በዝግታ፣ በጥልቀት ይተንፍሱ።
- ከሚያግዝዎት ሰው ጋር አይን ለ ኣይን ይተያዩ።
- ክፍል ውስጥ ያለ ነገር ላይ ያትኩሩ። ለምሳሌ ,ከተለጠፈ ማስታወቂያ ላይ ጥቃቅን ጽሁፎችን ለማንበብ ይሞክሩ።
- ራስዎን ያዘናጉ፣ የእግርዎን አውራ ጣት ብቻ ለማንቀሳቀስ ይሞክሩ።

ክትባት ከወሰዱ በኋላ ለአንድ ቀን ወይም ከዚያ በላይ ጤንነት ላይሰማዎት ይችላል፣ ነገር ግን ብዙ ጊዜ መለስተኛ ነው። እናም፣ በኮቭድ-19 በመታመምዎ ወይም በኮቭድ-19 ለተያዘ ሰው በመጋለጥዎ ኳራንቲን ማድረግ በማስፈለጉ ምክንያት ለቀናት ወይም ለሳምንታት ከትምህርት ቤት ወይም ከሌሎች ተግባራት ውጪ ከመሆን በጣም ይሻላል።

ልብ ይበሉ፣ ከ 18 በታች ከሆኑ ለመከተብ የወላጅ ወይም የአሳዳጊ ፍቃድ ያስፈልጋል። ወላጅዎ ወይም አሳዳጊዎ ከእርስዎ ጋር መሄድ ካልቻለ፣ ወደ ክሊኒኩ ደውለው ስለ ፍቃድ ሂደታቸው ይጠይቁ።

የኮቭድ-19 ክትባትን የሚያገኙባቸው ብዙ ቦታዎች አሉ። ከ 18 አመት በታች ለሆኑ ሰዎች ሁሉም የ ኮቭድ-19 ክትባቶች አይገኙም፣ ስለዚህ መሄድ የሚፈልጉበት ቦታ እርስዎ ሊወስዱት  የሚችሉት ክትባት እንዳለው እርግጠኛ ለመሆን ቀድመው ያረጋግጡ። www.vaccines.gov ላይ በአቅራቢያዎ ያሉ ቦታዎችን መፈለግ እና በክትባት አይነቶች መለየት ይችላሉ።

Minnesota Department of Health
Communications Office
PO Box 64975
St. Paul, MN 55164-0975
651-201-4989
health.communications@state.mn.us
www.health.state.mn.us

8/11/21 (Amharic)

*ይህን መረጃ በተለየ ቅርጸት ለማግኘት፣ ለሚከተለው ይደውሉ፡- 651-201-4989።*